4/0104/17
ነሐሴ 10 2016

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

**ጉዳዩ:- <u>በቁጥር 4/0074/17 ነሀሴ 03/2016 ዓ.ም የተላለፈ ውሳኔን ይመለከታል፤</u>**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር FXD/01/2024 ተከትሎ ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም በፊት እና በኋላ በዩኒ ሞዳል እና በመልቲ ሞዳል የትራንስፖረት ሥርዓት ዕቃዎች ተጓጉዘው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈጸምባቸው ጥያቄ የቀረበባቸውና በሚቀርብባቸው ዕቃዎችን በማመለከት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የጉምሩክ አገልግሎት ስለሚሰጥበት አሰራር በደብዳቤ ቁጥር 4/0074/17 ነሀሴ 03/2016ዓ.ም ሰርኩላር ማስተላለፋችን ይታወቃል።

የብሔራዊ ባንክ በየዕለቱ በሚያሳውቀው የውጭ ሀገር ገንዘቦች ምንዛሪ ተመን መሰረት ወዲያውኑ አስመጪዎች በዕቃዎቻቸው ላይ የጉምሩክ ሥነሥርዓት በመፈጸም መልቀቂያ ማግኘት የማይችሉበት በርካታ ሕጋዊ ምክንያቶች በመኖራቸው ምክንያት ቀደም ሲል በተላለፈው ሰርኩላር ላይ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም :-

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር FXD/01/2024 ተግባራዊ እንዲሆን ከገለጸበት ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም ጀምሮ የተመዘገቡ ዲክለራሲዮኖች ባንኩ በየዕለቱ ተግባራዊ እንዲደረግ በሚያስተላልፈው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት አገልግሎት እንዲሰጥ ።
2. የጉምሩክ ኮሚሽን የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል የብሔራዊ ባንክ በየቀኑ ያሳወቀውን የውጭ ምንዛሪ ተመን መረጃ ወዲያውኑ በጉምሩክ ስራ አመራር ስርዓት የመረጃ ቋት ላይ ያደራጃል፤ የኮሚሽኑ የሥራ ክፍሎችም በዚሁ አግባ አገልግሎት እንዲሰጡ፤
3. አስመጪዎች ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም በፊትም ሆነ ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም በኋላ የጉምሩክ ዲክለራሲዮን መዝግበው ከተሟላ ሰነድ ጋር ለጉምሩክ አቅርበው ሰነዳቸው ተጣርቶ እና ተቀባይነት አግኝቶ የዕቃ የስጋት ደረጃ ተወስኖ በተለያዩ ሕጋዊ ምክንያቶች በዕለቱ መልቀቂያ የላገኙ ዕቃዎች ሰነዳቸው በጉምሩክ ተቀባይነት ባገኘበት ቀን በነበረ ሥራ ላይ በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት የጉምሩክ አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲደረግ፤

4. የላገኙ ዕቃዎች ሰነዳቸው በጉምሩክ ተቀባይነት ባገኘበት ቀን ሀንቶ ሥራ ላይ በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት የጉምሩክ አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲደረግ፤
   አስመጪዎች ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም በፊትም ሆነ ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም በኋላ በተመዘገበ እና በሚመዘገብ የጉምሩክ ዲክለራሲዮን የትራንዚት ፈቃድ የተሰጠው እና የሚሰጠው ዕቃ፤ ዕቃው በትራንዚት ማጠናቀቂያ ቦታው ደርሶ ትራንዚት በማጠናቀቅ በአስመጪው የቀረበው ዲክለረሳሲዮን ከተሟላ ሰነድ ጋር መሆኑ በጉምሩክ ተጣርቶ ተቀባይነት ባገኘበት ቀን ሀንቶ ሥራ ላይ በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት የጉምሩክ አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲደረግ፤
5. ከላይ በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተገለፀው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሐምሌ 22/2016 ዓ.ም በፊት እና በኋላ በተመዘገበ እና በሚመዘገብ ዲክለራሲዮን በክፍልፋይ ጭነት ወደ አገር ለሚገባ ዕቃ እያንዳንዱ ጭነት በመዳረሻ የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በደረሰበት ቀን ሀንቶ ሥራ ላይ በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት የጉምሩክ አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲደረግ፤

ስለሆነም ከዚህ በፊት በቁጥር 4/0074/17 ነሀሴ 03/2016 ዓ.ም የተላለፈ ሰርኩላር በዚህ ውሳኔ የተተካ መሆኑ ታውቆ በዚህ ውሳኔ መሰረት የተሟላ መረጃ እየተያዘ ውሳኔው በጥብቅ ዲስፕሊንና ኃላፊነት ተፈፃሚ እንዲደረግ አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
ኮሚሽን ኮሚሽነር

ግልባጭ፡-
- ለጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ተቋማዊ ድጋፍ ዘርፍ
- ለጉምሩክ መረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት

  **ጉምሩክ ኮሚሽን**
- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ